


CamScanner

አንድ አምላክ በሚኾን በአብ በወልድ
በመንፈስ ቅዱስም ስም አምነን ቅዱስ ገብረ
ክርስቶስ በጽኑዕ ተጋድሎ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ እንደተገለጠለት የሚናገር በዕለተ ዓርብ
ርሚነበብ የብእሌ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ
ክርስቶስን ዜና ገድሉን በእግዚአብሔር አጋዥነት
እንጀምራለን ጸሎቱና በረከቱ ከእኛ ጋራ ይኹን
ለዘለዓለሙ አሜን ::

፩. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወደእርሱ መጣ
ከእርሱም ጋራ ቅዱሳን ሊቃነ መላዕክት
ሚካኤልና ገብርኤል ስዱክያልና ሰላትያል
አናንያል መጡ ::

፪. ዳግመኛም አዳምና አቤል ሴትና ኄኖስ
መላልኤልና ቃይናን ያሬድም አባታችን ኄኖክ
መጽሐፉን ይዞ ማቱሳላ ላሜሕ አባታችን ኖኅ
ሴምና ያፌት ካምም መጡ ::

፫. ከእነርሱም በኋላ የእግዚአብሔር ወዳጅ
አብርሃምና የክርስቶስ ምሳሌው ይሥሐቅ
የሥላሴ ማደሪያ የያዕቆብ ልጅ ጻድቁ ዮሴፍ
መጡ ::

፪. ከእነርሱም በኋላ ታጋሽ አዮብ የሞሠ ሙሴ ዓለሙ ኹሉ ቢመዘን የልብሱን ያህል የማይኾነው ካህኑ አሮን መጡ ። በመኻላቸውም እግዚአብሔር የሾመው ካህኑ መልከ ጼዴቅ ነበር። የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በዕዙሉ ቀን ፀሐይን የአቆመ ኢያሱም መጡ ።

፫. ዳግመኛም ነቢዩ ሣሙኤል የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ልጅ ሰሎሞን የኃያሉ የእግዚአብሔር አገልጋይ ጋድ ነቢዩ ኤልያስ ደቀ መዝሙሩ ኤልሣዕ መጡ ።

፬. ነቢያትም ጮሉ ነቢዩ ኢሳይያስ ከእርሱም ጋራ የነበሩት ዐሥራ አምስቱ ነቢያት መጡ። ነቢዩ ናታን ጥበበኛው ሚራክ ነቢዩ ኤርምያስ ነቢዩ ዳንኤል ነቢዩ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚያስተምር ዕዝራ ካህኑ ባሮክና ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ መጡ ።

፭. የነቢያት ልጆችም ኹሉ ሆሴዕና አሞጽ ሐጌ ሶፎንያስ ሚክያስ ዘካርያስ አብድዩ ናሆም ኢዩኤልና ሚልክያስ ዕንባቆምና ዮናስ መጡ።

፮. ዳግመኛም ከቡራን ዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት ከሰባ አርድእት ጋራ መጡ ። በመኻላቸውም

የምሕረት አማላጅ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነበረች ። ከእነርሱም ቀጥለው ቅዱሳን ኹሉ አባ ጳውሊ አባ እንጦንስ አባ መቃርስ ሦስቱ መቃርሳት አባ ሊኖዳ አባ ብስንዳ አባ አርሳኔ አባ በርሱማ አባ ዮሐንስ ሐፂር አባ ብሶይ አባ አጋቶን መጡ ። ዳግመኛም አባ ጳኩሚስ አባ አሮን አባ ዘካርያስ አባ አሞን አባ አብድዩ መጡ። ዳግመኛም ኤፍሬም አሞጽ አባ ስምዖን ዘዓምድ አባ ይሥሐቅ ሶርያዊ መጡ ። አባ አበከረዙን አባ ቴምድሮስ አባ አካውህ አባ ማቴምስ አባ ያዕቆብ መጡ ።

፱. ዳግመኛም የደብረ ቶርማቅ አባ ማርቆስና አባ ናትናኤል መጡ ። አባ ሣሙኤልና አባ ዳንኤል ንጉሥ የነበረ አባ አኖሬምስም መጡ ። ዳግመኛም የንጉሥ ልጆች አነበሩ አባ መክሲሞስና ዱማቴምስ መጡ ። አቡነ ዮሐንስና አባ መኪሞስም አባ አቡከናፍርም አባ በአሚንና አባ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት መጡ ። አባ ኤላሬምስና ጊዮርጊስ ሐዲስም አባ አብርሃም ሐዲስም አባ አድኅኔ መስቀል አባ ሳዊሮስና አባ ለጽጹን ቅዱሳንም ኹሉ መጡ ።

፲. ከዚህ በኋላ ቅዱሳን ሰማዕታት ጊዮርጊስና እንቶሪጦስ የዲያቆናት አለቃ እስጢፋኖስም መጡ ። ኒቆዲሞስና ጲላጦስ መስፍኑ ዮሴፍ ፀራቢና ቆጵርያኖስም ሃይማኖታቸው የቀና ብርሃናተ ዓለም ሦስቱ መቶ ዐሥራ ስምንቱ ሊቃውንት መጡ ። ቆዝሞስና ድምያኖስ አብረንዮስ እናታቸው ቴዎዳዳም መጡ ።

፲፩. ዳግመኛም አባ ጸንጠሌዎን ሰማዕትና በዋሻ የሚኖር ጸንጠሌዎን መጡ ። የሰገነቱ ሰው ዮሐንስና ቴዎቅሪጦስ መነኰስ አርከለዲስና ፊልሞና አብሳዲና አናኒቆስ ጳውሎስ መምህርና የኦሪት መምህር ገማልያልም ይኸውም በናድልዮስ የተባለ ቴዎድሮስ ነው የሕርማኖስ ልጅ ፊቅጦር ገላውዴዎስና የአንጾኪያ ሰው እስጢፋኖስ የጭፍሮች አለቃ ቴዎድሮስ የአርማንያው ጎርጎርዮስና ቅዱሳን ፵ ሐራ ሰማይ መጡ ።

፲፪. ዳግመኛም አትናቴዎስ ሰማዕትና አባ ሕርያቆስ አርሶኖፊስና ባስሊቆስ ጴጥሮስና አስክርዮስም መጡ። አጌኔስና ዮሐንስ ወልደ ፀራቢ ቂርቆስና ፊልሞን እርስጥፎሮስም አባ ኖብያ ዮሐንስ ዳኬዎስ ያስገደላቸው ሰባቱ ሕፃናትና ቅዱስ መርቆሬዎስ መጡ ።

፲፫. ዳግመኛም መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስና ነቢዩ ስምዖን ፈጣሪውን የዘነጋ ንጉሡ ሄሮድስ ያስፈጃቸው ዐሥራ አራት ዕልፍ ከአራት ሺህ ሕፃናትና ዕልፍ አዕላፋት መላዕክት መጡ። ንጉሡ ዳዊትም ዐጥንትን በሚያለመልም በአማረ ዜማ እየዘመረ ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ፤ ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይገባል። ለአብ ክቡር መባል ለወልድ ክቡር መባል ለመንፈስ ቅዱስ ክቡር መባል ይገባል ። ለአብ ሥልጣን ለወልድ ሥልጣን ለመንፈስ ቅዱስም ሥልጣን ገንዘቡ ነው ። ለአብ መመለክ ለወልድ መመለክ ለመንፈስ ቅዱስ መመለክ ገንዘቡ ነው ። ለአብ መንግሥት ለወልድ መንግሥት ለመንፈስ ቅዱስም መንግሥት ገንዘቡ ነው ። ለአብ ሰላምታ ለወልድ ሰላምታ ለመንፈስ ቅዱስ ሰላምታ ይገባል ። ለአብ ምስጋና ለወልድ ምስጋና ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል። ለአብ ዕጕት መባል ለወልድ ዕጕት መባል ይገባል ። ለአብ በዜማ መመስገን ለወልድ በዜማ መመስገን ለመንፈስ ቅዱስም በዜማ መመስገን ይገባል ። ለአብ ብሩክ መባል ለወልድ ብሩክ መባል ለመንፈስ ቅዱስም ብሩክ መባል ይገባል ። ለአብ ስግደት

ለወልድ ስግደት ለመንፈስ ቅዱስም ስግደት ይገባል እያለ በመልካም ቃና በገናውን እየደረደረ መጣ ። በዚህ ጊዜም ሰማያውያንና ምድራውያን ኹሉ ሰውን ለወደደው ሥሉስ ቅዱስ በእውነት ይገባል ብለው ሰገዱ ።

፲፩. ብእሌ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ በእውነት ይኹን ይኹን ይደረግ እያለ ከእነርሱ ጋራ አመሰገነ ። ስለፈጣሪው ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ብሎ ይኸን ኀላፊ ዓለም የናቀ የንዑድ ክቡር ብእሴ እግዚአብሔር ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ ጸሎቱና በረከቱ ከእኔ ..... ና ከቤተሰብኦቼ ከሕዝበ ክርስቲያንም ኹሉ ጋራ ይኹን ዘወትር በእየጊዜውና በእየሰዓቱ ለዘለዓለሙ አሜን ።



እግዚአብሔርን በዘገናና በመሰንቆ አመስግኑት (መዝ.፻፶)